

# ሻማ

ለእማ  - ለ - እ ማ ማ

ሻ _______________ ማ

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ሻ ______________ ማ
ባለ ሸማ።
ሻማ ______ ዛላማ
ባለ-ቃል ____ ለዛማ
ለእማ ______ ለእማማ።
ሻ _____________ ማ
ባለ ሸማ።
ሻማ ______ ዛላማ
ባለ-ቃል _______ ለዛማ
ለእማ ____ ለእማማ።

ሻማዋ መስዋትነትን ተሻምታ
ፍቅርን በዝቀሽ ሸምታ
***ተስፋን ቀለበች ፅናትን አቅንታ!***
ሻ _______________ ማ
ባለ-ሸማ።
ሻማ ______ ዛላማ
ባለ-ቃል ________ ለዛማ
የአንስትን እኩልነት አብርታ
ዕብለትን በሀቅ ንድፍ በሳስታ
ግለኝነትን፣ አፈርሳታ አውጥታ!
ሻ ______________ ማ
ባለ ሸማ።
ሻማ _____ ዛላማ
ባለ-ቃል ______ ለዛማ
ለእማ ____ ለእማማ።

ኀባጣን ሊታቃና
ኀሰኝነትን ልትቀጣ
የሚዷቅሳ አብራክ ልበ-ቀና!
አልሙ ማህፀን ልበ-ቀና!

ሻ _____________ ማ

ባለ ሽማ።

ሻማ _______ ዛላማ

ባለ-ቃል ________ ለዛማ

ለእማ _____ ለእማማ።

የሃልዬ እናት አውራ

የታማኝነት ልዩ ወጋግራ!

*ታህሳስ 29 ቀን 2001 ሄርሽን ሆቴል*

*ሥጦታ፡ ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር*




**ተፈታች የምልበት ቀን ገና ነው ...**

*ከሥርጉተ ሥላሴ*

የከበደን የሚያቀል አምላክ እንዲህ ያን ከባድ ሸክም አቃለለ። ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር

ከቃሊቲ እስር ቤት መውጣት ለጊዜው ... ታላቅ የመንፈስ ደስታ ነው። በአንጻራዊነት ወያኔ በቅድም ሁኔታ የፈተበት ሌላ መሰሪ ዓላማ አለው፤ ለእኔ። ሳንጃውም ሆነ ባርዱ የእሱ አይደል? ባለ ጊዜ፣ ሁለመናው እኮ የእሱ ንብረት ሆኗል። መንፈስን ሳይቀር ድንበር አልባ እየገዛ ...

ዜጋ እንደ ዜግነቱ ሳይሆን ነፃነቱን እንዲህ በጠራራ ጸሐይ ተቀምቶ፣ ተነጥቆ፣ ሰብናው ተደፍጥጦ መኖር። ይገርማል። ይህም ያልፍ እኮ ይሆናል። ብቻ እስኪያልፍ ግን እንዲህ ያሻል ይሰልቃል፤ ጊዜም ከባላ ጊዜ ጋር ይቃበጣል።

ለእኛማ የቃል አርበኛዋ፣ የጽናት ሐዋርያዋ፣ የጥንካሬ ተምሳሌቷ፣ የእኩልነት ማመሳከሪያ ቅኔዋ፣ የተሰፋ መጠጊያዋ፣ የብሩህ ራዕይ ዋቢዋ፣ የሚዛን ጠበቃዋ .... እንደ ገና ከአንደበቷ እና ከቅን መንፈሷ እንዲሁም ከብሩህ ህልሟ ጋር ያገናኘን አምላክ ይመስገን። አሜን! የፈለገው ዓይነት የወያኔ የለበጣ ትዕይንት የጀግናዋን ክብር፣ ፍቅር፣ ከቶም አይቀንሰውም። ከዚህ ላይ በልጅነቴ አንድ ያነበብኩት መጻህፍ ትዝ አለኝ። ይቅርታ ደራሲውን አላስታውስም ምን አልባት የወላጅ አባቴ የመንፈስ ጽኑ ጓደኛ የነበሩት ክቡር ደራሲ አቶ ከበደ ሚኬኤል ይመስሉኛል

“ ... የአንድ ሐገር ንጉስ ወደ አንድ የሚያስተዳድረው ከተማ ሕዝቤን ልጎበኝ ብሎ ይሄዳል፣ ንጉሱ ከከተማው ሲደርስ ነዋሪው በሙሉ ልብሱን አውልቅ እርቃነ ነብሱን ነበር፣ ንጉሱም ሕዝቤን ምን ነካው ይል እና ወደ ሌላው ከተማ ይሄዳል፣ ከዛም ተመሳሳይ ሁኔታ ይገጥመዋል፤ ሕዝቤ አበደ ማለት ነው ይል እና ወደ ሌላው አስተዳደሩ ይገሰግሳል፣ በዚህ መልክ ሁሉም ቦታ ልብሱን ያወለቀ ሕዝብ ይገጥመው እና ወይ ጉድ! ያበደው ሕዝቤ ሳይሆን እኔ ነኝ ብሎ እሱም ልብሱን አወለቀ ... “ ይል ነበር ታሪኩ ...

እውነት በተቀበረበት ሀገር አውነት ፈላጊ ወይንም የእውነት አርበኛ ወይም የእውነት ጠበቃ ወይንም የእውነት ቀንዲል፣ ምን ቦታ ይኖረዋል? እውነት እኮ ይሙት በቃ ተፈርዶበት የተቀበረው ቀድሞውኑ ወያኔ ሲፈጠር ነው። ወያኔ አሸዋ ሞልቶ እህል ነው እያለ የዓለምን መንግስታት ሳይቀር በለበጣ ያተለላ የውሸት አዛውንት ነው።

... በሌላ በኩል ደግሞ አንዲት ፍሬ ንፁህ ሰንዴ ከእንክርዳድ መሐል .... የክብርት ዳኛ ብርቱካን እውነት ፈላጊነትም ህልቆ መሳፍርት ለሌው የወያኔ የቁጥጥር ሰንሰለት እንዴት እና እንዴት ብሎ ሊታረቅ ይችላል? ይህን ሀቅ በስልት እና በማስተዋል ሆናችሁ ተመልከቱት .... ውሸት በነገሰበት ሐገር እውነት እስረኛ ነው።

ያለው አማራጭ መሰሉን ውሸት ከመሰሉ ጋር ማገናኘት ነው። ድስት ካለ ድስትፊያው አይሆን? ለጠቅላይ ሚ/ሄሮድስ መለስ አሰተዳደር የውሸት ድስት አውነት ልኩ አይሆንም ስለዚህ በመሰሉ የውሸት ድስት እፊያ ግን ልኩ መጠኑ ስለ ሆነ አታሞውን ሲያሰደልቀው አውሎ ያሳድረዋል። ውሸት ለወያኔ ጣእሙ። አፍ መሻሪያው፣ መርከሻ መዳህኒቱ ነው። የወያኔ ደመኛ ጠላቱ ደግሞ እውነት ነው። ወያኔ መስሎት እንጂ እውነት ጊዜውን ጠብቆ መውጣቱ አይቀርም።

ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ ጽናትን ሰንቃ፣ ጽናትን ታጥቃ፣ ጽናትን አስተምራ፣ ጽናትም ሆና አሳይታናለች። ጥንካሬዋ ብርታቷ፣ ፍጹም የማይበገርው ነፃነት ፈላጊነቷ ሁልጊዜም ለትውልዱ ታላቅ የተግባር ተቋም ነው። በወጣትነት ዕድሜ ሊገጥሙ የሚችሉ መንፈሳዊ ሆኑ ሥጋዊ ፈተናዎችን እረታ ለእድሜ ልክ እስራት ብይን ስትበቃ ቃሏን ጠብቃ፣ የተግባር ጀግንነቷን በድርጊት አቅልማ ነው። ስለዚህ የወያኔ ቅልሞሽ ከቶውንም የእኛን መንፈስ አሸንፎ አሳስታናለች ብለን ልንቀበለው ቀርቶ ልናስበው እንኳን ከቶ አንችልም። ትናንትም ዛሬም ነገም ከነገ ወዲያም ስለ እንቋችን እንመሰክራለን። እንነገራለን። ከጎኗ ሆነን ዓርማዋን እንከተላላን። ይህን ማድረግ ሲሳነን ያኔ ወያኔ አሸንፌያለሁ ብሎ ይደልቅ፤ አሁን ግን በፍጹም! ለእሱ በዕብለት ለባዘነ - ለወዬበ - ለዛገ - ሐሺሺ ላባዘተው ህሊናው ብቻ ለበጣውን ይቀልበው።

ክብርትነቷማ ሁለገብ ብቃቷ ከትህትና እና ከውስጥ በሚፈለቅ የንጽህና ንጥር ስለሆነ ለጥቂት ደቂቃዎች ከእሷ ጋር በመቆዬት ብቻ መንፈስን እንዳሻው የመገራት ልዩ መንፈስ ያላት በመሆኑ በፍቅር የመንፈሳችን አስተዳዳሪ ናት። ይህንንም እኔ ሥርጉተ በስማ በለው ሰምቼ ሳይሆን እራሴ ድርሶብኝ አይቼዋለሁ። ሁለመናዋ ፍቅር ነው እና።

እርግጥ ነው ደስታ ቀላል በመሆኑ ብቻ በቃል ተገለጸ፣ እንጂ ምጡ ምጥ ነበረ፣ እንዲህ ከነሙሉ ጤናዋ፣ ከነሙሉ አካሏ እንደ ገና ያገኛኘን አምላክ አሁንም የተመሰገነ ይሁን። ምንም እንኳን ድርጅቷ አንድነት የተገባውን ያህል ጉዳዮን በባለቤትንት ባያሰተናገደውም፣ የቅንነት አማላክ አረሳትም እና ከወላጅ እንቷ ከወ/ሮ አልማዝ ገ/ማርያም እና ከሃሌ ሚዲቅሳ፣ እንዲሁም ከሚወዷት፣ ከሚያከብሯት፣ ከሚሳሱላት ወገኖቿ ጋር ለመገናኘት በቃች

ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዴቅሳ የከፈለችው መስዋእትነት ማናኛችንም ቢሆን ቢደርስብን ላንደርገው የማንችለውን ነው እሷ የከወነችው። ከበቂ በላይ፣ ከተገባት በላይ ታላቁን ተገድሎ ፈጽማለች። ከእንግዲህ በኋላ ከእኛ እንጂ ከእሷ የሚጠበቅ ቅንጣት ነገር ከቶውንም አይኖርም። እርግጥ ነው ለእኔ አሁንም አልተፈታችም ሰንሰለቱ ከቃሊቲ ወደ ፈረንሳይ ሊጋሲዮን ነው የተዛወረው። ... **ተፈታች የምልበት ቀን ገና ነው።** ለነገሩ ትልቋ እናት ሀገር ኢትዮጵያስ እስረኛ አይደለች?!

በተረፈ እስኪ በምልሰት በኮንፒተር ብቻ የተጻፉትን ... የትናንትነዋ ጀግና ዛሬም ለድህረ ገጻችን ለጸጋዬ ድህረ ገጽ እንዲሁም ለጸጋዬ ራዲዮ ጀግና ናት እና እንሆ ...

## ሚዛኗ የት አለች?

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ለዓላማዋ አደራ፣ እድፍ ታጠራለች
ዕብለትን ሰንጋ፣ ለሀቅ ተሰውታለች

ሰንደቅን አድምቃ፣ ትውፊት ታፈልቃለች
ትናንት እና ዛሬ እሷ ትቀልጣለች።

ሚዛኗ  የት አለች?

ዓይናማ በመሆን፣ ፈር ቀዳጅ ሆናለች
መሆንን በመቻል፣ በተግባር ከብራለች
ጽናትን አቅልማ፣ ትእግስት አጥብታለች
ከብርቱካን ጋራ ይኸው ተጋብታለች።

ሚዛኗ የት አለች?

ቃሏን በመጠበቅ፣ ቋሳን ፈትሻለች
እንክርዳድ ከስንዴ አንተርትራዋለች
ፋሽስተን አጋልጣ፣ ቀያፋን ልጋለች
ሰንሰለት ላይ ሆና ብርሃን ልካለች።

ሚዛኗ የት አለች?

አንድነት ፀንሳ አብሮነት ወልዳለች
ቀድማ በመገኘት ደወል ደውላለች
እራሷን ሰጥታ ጧፉን ለኩሳለች
ብርቱካን ፍሬዋን ይሄው አፍርታለች።

ሚዛኗ የት አለች?

የተበተነውን ልቦና ገርታለች
ትግሉነን በመኳል፣ መቀነት ታጥቃለች

ለኢትዮጵያዊነት ኪዳኑ፣ ድርሳኑ፣ ቀለበት ሆናለች
ብርቱካን እመቤት ለኛ ትሆናለች።

ሚዛኗ የት አለች?

ክህሎትን በዕድምታ ትመግበናለች
በህሊና መንፈስ ታታግለናለች
ተስፋነን አብቅላ በአንድነት መርታለች
ፍቅርን ሸማ ሥርታ በምዕላት ድራለች።

ሚዛኗ የት አለች?

ጨረሯ ዓለም ሆኖ ጧፉን ለኩሳለች
ለሙያዋ ፍቅር ልዩ ዓምድ ሆናለች
ከዳኛዋ ዘንዳ ከሷ ትገኛለች
ከብርቱካን ጋራ አብራ ተፈጥራለች።

ሚዛኗ የት አለች?

የእማን ጡት ፅንሷ አድርጋለች
ከብርቱካን ጋራ ዕውነት ገብራለች
ለሀገሯ ትንሳኤ ትንገበገባለች
በፈርኦን እግረ ብረት ትርገበገባለች።

ሚዛኗ የት አለች?

ሀቅን ትፈትላለች
ሞትን ሳትፈራ ቅደመኝ ብላለች
የወሰነችውን፣ የቆረጠችውን ትቆረጥማለች
ዕጣችን - ክፍላችን ንባችን ሆናለች።

ሚዛኗ የት አለች?

የግንባር ሥጋዋ እሷ ትሆናለች
ከጣይቱ ዘንዳ መክሊትን ወርሳለች

ፀጋችን በመሆን ቁርጡን ነገራናለች
የሲና ወርቅ ሆና ሁሌ ታበራለች።

ሚዛኗ የት አለች?

የቀዘቀዘውን እሷ ታደምቃለች
ምርኩዛችን ሁና ትደግፈናለች
ትውልዱን በተግባር ታደራጃዋለች
ብርቱ አትጠገብ - እሷ ለኛ ሆናለች።

በዓይነ ህሊና ትመጣብናለች
በ መንፈስ ሰንሰለት ትናኘናለች
በአንድነት ድልድይ መንገዱን መርታለች።

የ አንበሳ አብነት ህውልትም ሆናለች
ሥረ ጉባኤአችን፣ ቅኔአችን ቃናችን ...
ዳኛችን ሆናለች!

*ሥጦታ፣ ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአድነት ሊቀመንበር*

*ታህሳስ 29 ቀን 2001ዓ.ም ሄርሸን ሆቴል*

**መከሊታችን - የተስፋ ጉዞአችን ናት**

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ተስፋ - ጉዞ
ተስፋ - ራዕይ
ተስፋ - መንገድ

“ግፉ መሸከም ከምችለው በለይ ሆነብኝ።” ክብርት ዳኛ ብርቱከን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር። እውነት ለመናገር ከሆነ ... በታሪክ በዚህ የዕድሜ ክልል ለዛውም ሴት ሆኖ ይህን የመሰለ የከበረ ፀጋ የተጎናፀፈ የለም። ብንፈልገውም አናገኛውም። በፆም በፀሎት - በሰጊድ አይገኝም ሲታደሉት ብቻ ...

ምንም እንኳን የጠ/ሚ/ሄሮድስ መለሰ ዜናዊ አይሁዳዊ አመራር እና የግፍ ጫና በክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ ላይ እጅግ የመረረ እና ጎምዛዛ ግፍ፣ እንደ ሰውነቷ ቢከብዳትም ... ለእኔ ግን ይህ በራሱ ለተመረቁት ብቻ - ለተመረጡት ብቻ የሚሰጥ ልዩ ረድኤት ነው።

እና በረከቱን በሰው ሰውኛ አንተርጉመው። ሰማያዊ ነው እና! ግን አታስቀናም - ተጋድሎዋ?! ... ቆራጥነቷ ... ፅናቷ ... ብርታቷ ... አርቆ አሳቢነቷ እንዲህ በዓለም ሲያበራ! የዓለም ዓቀፉን መህበረሰብ በአክብሮት ሲገዛ፣ ኢትዮጵውያንን በፍቅር ሲነዳ፣ ፋሺስታዊዉን የፈርዖን አስተዳዳር እርቃኑን ሲያስቀር፣ እነ ቀያፋን ከባህረ የወጣ አሳ ሲያደርግ፣ ቃልን ለወግ ለማእረግ ሲያበቃ፣ እልህን ወልዶ መንፈስን ሲያስተዳድር እና ለወገኖቿ ህሊና የፅናት ወተት ሲያጠባ ከቶ ከዚህስ በላይ ምንስ መታደል አለና!

ሞት ምንድን ነው? መኖርስ ምንድን ነው? ትግልስ ምንድ ነው? ለጀግንነት ካልሰገደ - የህዝብን ጥቅም ካላስቀደመ - ድፍረትን ካልመገበ - ስምን ከመቃብር በላይ ካላዋለ። የማከብራችሁ ምንም ታውቃላችሁ? ... ምንም ነው። እሷ ግን እራሷ ሰንደቅ ናት። እራሷ የመንፈስ ቀለበት ናት። የተስፋ ኪዳን ናት። የፅናት ውል ናት። ዳኛ ብርቱካን በራሷ ኀለጎታ ናት።

መድህኒታችን እዬሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ካለ እናት ዓለምን ካስተዳደረበት ዘመን ድህረ ዓለም ካለ አባት በድንግልና ተፀንሶ ድንግልናዋ ሳይገሰስ በቅድስት ድንግል ማርያም በአጭር ቁምት እና በጠባብ ደረት ተወስኖ በመጀመሪያ የነበረው ቃል ሥጋ ሆኖ በተዋህዶ ከብሮ ሰው አምላክ - አምላክ ሰው የመሆኑ ሚስጥር ...

... መከራችን፣ ፍዳችን፣ ስቃያችን በምድር ላይ ሆኖ እንደ ሰውነቱ መጋራቱ አባታችን እንድንለው፣ ቅርብ - ጥግት እንድንለው አደረገን። የሰማይ እና የምድር ንጉሥ፣ የሰማይ እና የምድር ልዑል የሰማይ እና የምድረ ጌታ፤ ሆኖ ግን ነገር ግን **አንተ** አልነው። የልባችን ነገርነው። ሳንፈራው። እንደ አምላክነቱ ደግሞ የረቀቀውን የተዋህዶ የዕማድ ሚስጥራትን፣ አምላካዊ ትግስቱን፣ ዕርገተ ህብስቱን አሳየን - አስተማረን። የሃይማኖት አርበኞች ሐዋርያት፣ ፀድቃን ሰማዕታት፣ ደናግል መናኩሳት የሱን አብነት ተከትለው በህይወት ኖሩ። የመጨረሻውንም አክሊል ተቀዳጁ።

አዎን ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳም እንደ ህግ ባለሙያነቷ ለትክክለኛው ዕውነተኛ ሚዛን ጥብቅና ቆመች። ለህግ የበላይነት በፅናት ቆመች። ሆና አሳየችን። በቃል ሳይሆን በድርጊት ሰበከችን። ራሷን ለስለት ሰጥታ ሙያዋን ሰንደቅ አደረገችው፣ አስከበረችው። <u>ዳኛ ብርቱካን የተሰፋዋ ሀገራችን የጉዞ ማሾአችን ናት። የራዕያችን ባትሪያችን ናት። የህልማችን ብርሃናችን ናት።</u>

እንደ ማንኛውም ሰው የተደላደለ ህይወት፣ ለዘውም ሥራ አማርጣ መኖር ስትችል ... የእናቷን የማህፀን እንባ ... ሳትረግጥ፣ ሳትጨፈልቅ፣ ሳትደፈጥጥ ይልቁንም በርከክ ብላ ሰገዳ ከእማ ለእማማ ... ከህሊናዋ ከዕምነቷ፣ ከተሰፈዋ፣ ከፍላጎቷ እና ከራዕዮ ጋራ በሥርዓት ተጋብታ ቀለጠች።

... ቀለጦው ግን ለአፍሪካ ሴቶች መቅድመ - ቀንዲል ሆነ። ለዝንትዓለምም በህይወት እስካለን ድረስ ጥንካሬዋን፣ ብርተቷን፣ ወኔዋን፣ አልገዛም - አለንበረከክም ባይነቷን በዝክረ መወደስ አናቅሰዋለን ... <u>የሴቶች እጨጌ ናት እና!!!</u>

በሌላ በኩል ደግሞ ውጪ እንደምንኖረው ወገኖቻ ቢያንስ በነፃነት መኖር ስትችል፣ ካለ ምንም ችግር ታግላ ማታገል ስትችል አጋጣሚው እያላት ... በህሊና ዳኝነት መኖርን መረጠች። እስኪ መዳህኒዓለም ይጠብቃት።

ገዥ መሬት ላይ ያለውን፣ በስልጣን የዳበረውን እናም በአጋዚ ሠራዊት ጥበቃ ከሚደረግለት ፋሽስታዊ አስተዳደር፣ ጋራ በእናት እንቷ ፍጹም ጸጋ በሰላማዊ መንገድ የሕዝብ ሁነኛ፣ አለኝታ ለመሆን ብሶትን ተጋራች። ችግሩን አዳምጣ ዋይታውን ተቃመሰች፣ መከራውን ተሻምታ መራሩን የሀሞት ዘመን በተደሞ ተጋራች።

ከእራሷ፣ ከልጇ፣ ከወላጅ እናቷ፣ ከቤተሰቦቿ የብዙኃኑን የሕዝብ ጥቅም ... የተስፋ ጉዞ አስቀድማ በፍል እየተንገረገበች፣ በወለፈን እየተለበለበች፣ በጋለ ምጣድ እየተንገረገበች ***በቋሳ ተጨቀጨቀች።*** እንደ እናት እናቷ ደግሞ የእናትነት ድርሻዋን ተወጣች።

እናት ... ፈርጥ የህይወት፣ ጌጥ የኑሮ፣ መደህኒት የመንፈስ፣ በኩራት የተስፋ፣ አስራት የሁለመና ናት። እናት ገለፃው ሁሉ እናት ያንሳታል። እና ክብርት ወ/ት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊ/መንበር የእናትነትን ሥነ-ምግባር ሙሉውን ነው የፈፀመችው ለእኔ ለሥርጉተ ።

የእናት ሀገራችነን ውስጥ ውስጧ በማድረግ <u>ቀድማን በእውነት ቀድማን፣ በልጣን በእውነት በልጣን ለሰነሰለት እና ለሞት ፈጥና ገሰገሰች።</u>

ዳኛ ብርቱካን ሚስጥር ናት!

ዳኛ ብረቱካን የተስፋ ጥበብ ናት

<u>ዳኛ ብርቱካን የብርሃን ምንጭ ናት። ከቀስት እናመልጥ ዘንድም የተሰጠችን የባንዴራችን፣ የአንድነታችን ሁነኛ ዋቢያችን ናት። ህበር ናት; የፍቅር ድሪ ናት። የመቻቻል አልቦ ናት። የሁኖ መገኘት አሸን ኪታብ ናት። የፅናት ደግሞ ባላ ናት። የነፃነታችን ፋና ናት። የተግባር ልዕልት ዕንቁ ፍጥረት ናት።</u>

ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር .. መከራን መርጣለች፣ ድሎትን ገፍታለች ኃሳርን መርጣለች፣ ምቾትን ገፍታለች መስዋዕትነትን መርጣለች፣ ለራስ መኖርን ገድላለች።

ጨለማን መርጣለች ...

ብርሃን ታድላለች

ተስፋን አልምታለች

ጉዞን ቀይሳለች

ህብረት ታጠባለች

አብሮነት አቅልማለች

ለሰላም ታግላለች

ፍቅርን ታውጃለች።

እሷ እራሷ ... አስተውሉ እሷ እራሷ በጨለማ ውስጥ ያለች **ፀሐያችን** ናት። አይደለችም ናት ደፍረን እንናገረው። ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ ... የማንነታችን ዘውድ - የእኛነታችን ተክሊል፣ ለሰንደቃችን ብቁ አርበኛ፣ የሁለመናችን አብነታችነ ናት። ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የሁለመናችን ሁለመና ናት። ክብርት ወ/ት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ ለትውልዱ የፀረ ወንበዴ ትግል በአንድምታ ልናመሳጥራት የሚገባ ***<u>የመንፈስ ሚስጥር</u>*** ***<u>የመንፈስ ቅዱስ መከሊታችን ናት።</u>***

**ሴቶች የተግባር እመቤቶች ናቸ!**

**ሴቶች የትውልዱ መሰረቶች ናቸው!!**

## ባለ ማተቧ ህግ ናት

*ሥርጉተ ሥላሴ*

እንዴት ሰነበትሽ እመቤቴ?

ልዩዋ አንባር የማንነቴ።

ራዕዮ - ዬመብቴ

የአርነት - ምልክቴ

እንዴት ሰነበትሽ እመቤቴ?

የሁለመና - ትንግርቴ
የእኩልነት - ታምራቴ፤
የድንቅነሽ ልዕልቴ

መሰረቴ
እንዴት ሰነበትሽ እመቤቴ?

ማዕረገ-ጸዳል ክብርቴ
ክብረት የጠነከርሽ ብርታቴ
የፍቅር ቤቴ የእትብቴ፤
መስታወቴ
እንደምን አለሽ እመቤቴ?

የሃቅ ተቋም መሰረቴ
የተግባር ድጓ ታቦቴ፤

የእኩልነት መስኖ ልማቴ
አንችው ቀለጥሽው ለደህንነቴ?
እንደምን ሰነበትሽ እመቤቴ?

የቃል ቤተኛ ህብረቴ
የድርጊት ጀግና መብራቴ
የተጋድሎ ክታብ ስስቴ፤
የጥንካሬ አልማዝ ቀለበቴ
እንደምን አለሽ እመቤቴ?

የብቁ ዝናር ሃውልቴ
የክፉ ቀኗ የእናቴ
የወርቅ እንክብል እርስቴ፤

እንቁዋ እህቴ
እንደምን አለሽ እመቤቴ?
የአናብስት አለቃ ጉልላቴ።

የጥሩ ዘር ውብ ቀለም፤
ለዛዋ፣ ለ ዘ ለ ዓ ለ ም
ለሕዝብ ዕንባ ያላለች ዝም?

ፀሐይ ናት እሷ  ኮከባችን
   የጽናት እንብርት ንጋታችን፤
      የአዲስ  ምዕራፍ  ከፋቻችን
የውል የኪዳን ብሥራታችን።

የመርገምት ሥርዬት ቀንዲላችን
  የአንስት  አብነት ዋናችን
   ለእኛ የሆነች አስራታችን፤
      የዕንባ ህላዊ በኩራታችን ...
የቆራጥነት ፈለጋችን።

እመ ትእግስት ማሾ-ችን
  ውስጧን የሰጠች ለእናታችን።
      የጀግኖች ጀግና ቀንድ ናት
ባለ ማተቧ ህግ ናት።

*ሥጦታ . ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዴቅሳ ለአንድነት ሊቀመንበር*

*ሚያዚያ 15 / 2001 ዓ.ም  ሄርሽን ሆቴል /ሲዊዘርላንድ/*

## ፅናት

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ዓውራ! ወጋግራ! ዓምደ ብራ የሚያበራ የሚገራ ፍርኃትን፣ ስጋትን፣ ጭንቀትን የሚመክት። የውስጥ ደም ፈተናን የመቋቋም አቅምን፤ ብቃትን፤ ልኬታን የሚበይን ክቡር ሥነ ምግባር ነው። አጥንትን ስርስሮ የሚፈትሽ። እራስን በእራስ የሚዳኝ።

መብላትም መጠጠትም፤ ድሎትም መከፋትም፤ መኖርም ማለፍም ሁሉም በጊዜያቸው መዋዕለ ዕደሜያቸውን ተከዘው ይበናሉ ይተናሉ። የሕይወት ዥንጉርጉር ገጠመኝም እንደ ዕጣ ፋንታው ሊመንን ወይ ሊመነኩስ ወይም ዓለምን መስሎ ሊያድር ይችላል።

ሐገራዊ ብቃትን የሚመዝኑ ችግር እና መከራን ተቋቁሞ ለሚያልፍ ዕድሜ፤ ለዕልፍ የደም ዕንባ  ዕልፍ ብሎ ኃሳርን በፀጋ እና በሐሤሴት መቀበል፡ አልፎ ተርፎም ሞትን ቅደመኝ ብሎ በቃል መፅናት ግን የሰንደቆቹ ሁሉ ጉልላት ነው።

ቃል ቃል ነው። ቃል ቃልነቱ ቃል ሆኖ ፋና የሚሆነው ግን ቃል አሳለፊው ለቃል ኪዳኑ ሲያደገድግ ሲሰግድ ቃሉን ለቃሉ በተግባር ሲያሰጌጥ ብቻ  ይሆናል።

ይህ ደግሞ የሁለመናን ክብረት የተሰራ ፅናትን ይጣይቃል። ወጀብ፤ ዓውሎ፤ ጎርፍ ሳያሸንፈው፡ እንደ እንሰሳ ለከርስ ሳያድሩ መፋለምን፤ መቁረጥን፤ መወሰንን ይጠይቃል። ግለኝነትን ድል ነስቶ ለሚሊዎን ብሶት ዘብ መቆምን ይጣይቃል እራስን ይፈትናል ያፋጥጣል።

__*ፅናት*__ *ታማኝነትን አፍልቆ መሆን መቻልን ይገብራል። ግልብ ስራሽን ውስጥነት አንጠሮ ምልከት ዓርማ ይሆናል። የሴልን የነርብን የጅማትን ህዋስ እንደ ወረቅ ያነጥራል። የመስዋትነት ቃና ዘጉባኤ ይሆናል።*

*ፅናት ማንነትን አጉልቶ እራስነትነ ይተርጉማል። ከዘማናችን ብርቱ፤ ጠንካራ፤ ታታሪ መሪዎች አንዷ ብረቋ ከሆነችው ከጀግናዋ ዳኛ ብርቱከን ሚዲቅሳ ያገኘነው ዘመን የማይሽረው፤ ወቅትታት የማያ-ወይቡት፤ ጊዜ የማያፋድሰው የሀቅ እንክብል ይህ ነው።*

*ስለሆነም ትውልድ ለማይተካት ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር በተግባር ያጌጠ መከራን በፍቅር ተቀብሎ ላስተናገደ ጀግንነት ..... የመታገያ የጋራ ዓርማችን ነው።*

*ጀግንነት ፋሽስትን ድል ነሰቶ ህዝባዊ ፍቅርን በምዕላት በእያንዳንዳችን ህሊና ሲከትም በዕድሜዬ ያዬሁት በብርቴ ነው። ስለሆነም „ውረሰ ጽናትን“ በልቦናዬ አብቅሎ ያለማ ዘንድ መዳህኔዓለም አባቴን ተንበርክኬ በአፅሀኖት እለምነዋለሁ።*

*ዳኛ ብረቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር የቃል አርበኛ፤ የነጻነት አብዬተኛ፤ ሁነኛ፤ አሥራት፤ የጽናት ጉልላት የእኩልነታችን ሰንደቅ ፋና ወጊ ናት።*

*በውስጤ ያለው የፅናት ራዕይ በህሊናዬ ዙሪያ ቋሚ የሆኑ ተግባራትን ያካትታል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ በሲዊዘርላንድ በዙሪክ ከተማ ራዲዮ ፕሮግራም መጀመር ነው። በሌላ በኩል በድህር ገጹም የተገባውን ያህል አትኩሮት መስጠት።*

...

**ካለ ሴቶች ንቁ እና ብረቱ ተሳተፎ የፀረ ወያኔ ትግሉ ዓላማ እግቡ አይደርስም!**

**ወርቅን ያነጠረ ፅናት የዕድሜ ልክ ዕንቁ ነው!**

**ነፃነት በወያኔ እስር ለሚማቅቁት ለክብርት ዳኛ ብረቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር እና በወይኔ እስር ለሚመቅቁ ወገኖቻችን ሁሉ!**

**ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኑር!**

## ቀለሜ

*ከሥርጉተ ሥላሴ*

ቀለበቴ ማተቤ ናት

ተቋሜ፣

የጽናቴ ቀለሜ።

ጥልቀቴ ናት ድሪዬ

የጀግንነት አዝመራዬ።

መንፈሴ ናት መሪዬ
ለዘመናት ጉልላቴ።

ሚሥጢር-ክታብ፣ አሻራዬ
የእኩልነት ዋቢዬ።
መኩሪያ ናት ጥላዬ
የእንባ ጋሻ ከለላዬ።

ማርከሻ ናት ጀግና፣
በተግባሯ ገናና!
ሙሉ ልቅም ሰብና
ከድርጊት ጋር የተስማማ።
ዝልቅ ምግባር ሙና
ፊት የሆነች - የግንባር ሥጋ።
መንፈሷ አለው ከነጻነት
ረቂቅ፣ ውለ-ሕይወት።
ዝም አትልም ትፈካለች
ወርቅ ናት እና ታበራለች።

ብረት አለው ትእግስቷ
የብርቱዋ ሰንሰለቷ።
ሁሌ ቁማ የማትዝል
አትደከም ዝንፍ አትል።
እንደ አደረች - ለአንደበቷ
የአደራ ቃል መሰረቷ።
ሁሉን ችላ አሳልፋ
ታፈልቃለች - እንደ ገና!
ሃብታችን ናት የማንነት
ለእኩልነት - ለአርነት።
አደራህን! መዳህኒዓለም - ጠብቅልን
ፈርጣማዋን አብነትን።

*ሥጦታ ... ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር*

*ጳጉሜ 3 ቀን 2002 ዓ.ም ቪንተርቱር - ሲዊዘርላንድ።*

## ትታያለሽ

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ታበሪያለሽ
ታስውቢያለሽ
ብርቱ ሀቅን ታነጥሪያለሽ።

ታፅናኛለሽ
ትራሪያለሽ
ትመክሪያለሽ
ብርቱ ለእኛ ታፅነቢያለሽ።

ጥንከሬ ታመርቻለሽ
ታሪካችን ትፈጥሪያለሽ
ሴትነትን ታስውቢያለሽ ...
ጀግንነትን ታጎያለሽ!

ምሰሶችን ...
ባላችን ነሽ ወጋግራችን ...
መመኪያችን
ዋቢያችን ነሽ ...
ለእኛ ብለሽ ትቀልጫለሽ
ፍፁም ልቀሽ ትታያለሽ።

*ሥጦታ፣ ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ ለአንድነት ሊቀመንበር*

*የካቲት 24 ቀን 201 ዓ.ም ጀርመን - ሙንሸን*

**ይድረስ ለአናብስት ፋና!**

****                    ***

*ሥርጉተ ሥላሴ*

*ስስት እንደምን አለሽ? ናፈቆት እንዴት ሰነበትሽ? ዓይን እንደምን አለሽ?*

*አንቺ የግንባር ሥጋ እንደምን ነሽ። አንች የቃል አርበኛ እንዴት ከርምሽል?*

*አንች የፅናት ሁነኛ መከራው፤ መከፋትሽ፤ ጉስምታው እንዲያው ከሁሉም በፊት*

*ያ የምትወጂው የህግ የበላይነት ጥረት ናፈቆት እንዴት ያደርግሻል?*

*አንች የሚዛን ጠበቃ፤ ሚዛን እራሱ እንደ ... ሚሳሳልሽ ታውቂያለሽ? የብዙኃን መድረክም ... ሱባዔ ላይ እንዳለም ልነግርሽ እወዳለሁ። ሰግቷል፤ ፈርቷል ... በምናቡ ይሁን በዕውኑ ከአንቺው ጋር ነው። እርበሽዋል። ጠምትሻዋል። የፆም አውሃ ሆንሽበት። እባክሽ በሞቴ ዓይንሽን ለአፍታ ለአንዲት ሰከንድ ይማፃንሻል። ትችያለሽ ... አቅም አነሰሽ አይደል?! ... ለነገሩ በአርዮስ እጅ ወድቀሽ እንዴት ትችያለሽ?? ? ?*

*ታናገሪው ዘንድ፤ ታዋያይው ዘንድ ቃናሽን ታሰሚው ዘንድ ይለምንሻል። **አንቺ ቅኔ የዕውነት ቅኘት። የቆራጥነት ዝማሬ! የድፍረት ንባብ። የቃል አቋቋም። የብርታት ድጓ፤ የተስፋ ምዕራፍ። የእኩልነት ዋዜማ!** ከቶ እንድምን አለሽ? ህልምሽ ከነክብሩ ከአንቺው ጋር ክልትምትም፤ እንግልትት አለ። ግንስ አንቺው አለሽለት። ... ሆድዬ በበለኃሰብ እጅ ከወደቅሽበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ተንበረከከ፤ እንዳ አነባ ይኸው አለ? ሚዛን ....*

*እኔም ብለምነው ... ብለምነው አሻም አለኝ። አሻፈረኝ አለ። እረሀቡ ጥማቱ ገደለው። ምን? ... እደሚለኝ ታውቂያለሽ "እሷም ችላዋለች እንኳንስ እኔ፤ **የታሰረ አየር** እየተነፈስኩ። ይልቅስ፤ ... ለዋስሽ እሰቢ፤ ፁሚ ... ፀልይ ... ስገጂ ... ውደቂ አምላክሽን ታደገን በይው .. አሳስቢው። ይለኛል ... ይለኛል ... ይለኛል ... መሃለቁ የእሷ ነገር እንጂ ... ደግሞ ለቋሚ ለእኔ ... ታስቢያለሽ?! አርፈሽ ተቀመጪ። ...*

*መስዋትነቷ እንዳይሸጥ፤ እንዳይለወጥ፤ የቅርጫ ... እንዳይሆን ጠንክረሽ፡ በርትተሽ አረመኔዎችን ተሞገቺ። ታገያቸው። ወለላሽ እንቅልፍ አልቦሽ፣ ነፃነት አልቦሽ፤ .. ሙብት አልቦሽ ሆና ተሰቅዛ ተይዛ ... በይ ለእሷ ታጠቂ! ... ተነሽ! ፋታ ንሺው! ...*

*ይለኛል ... ይለኛል ... ተሸክምሽ የምትዞሪያት ብዕርሽ ትናገር፤ አናገሪያት ዱዳ እንዳትሆን አደራን ታብራ ... ለሙብት ... ለነፃነት ... ለባንዴራ ... ለሀገር ... ለህዝብ፤ መተንፈሻ ባንቧ ትሁነን። ወታደር፤ አርበኛ፡ መለዮ ያላት አድርጊያት ... __**ዓርማዋ ዕውነት ይሁን።**__ ይለኛል ... ይለኛል ...*

*ጊዜ አይታ ከባለ ጊዜ ጋራ እንዳታሽረግድ፤ እንዳታረገርግ፤ እንዳትዛነፍ፤ ግርድፍን ትግራ! ትግራ ... ትግራ! ሽካራን ትሞርድ። ትሞርድ! ... ትሞርድ! ... ኮረኮንቹን ትደልድል። ወጣ ገቡን ታረቅ። ከሀቅ ጋር ታዘምር። የእሀቷን አሳር ትጋራ ... ትጋራ! ትጋራ! ይለኛል ... ይለኛል ... ይለኛል ...*

*የእንባዋ አጋፈሪ ትሁን አብራ ታንባ። ሰቀቀኗን ቀለቧ ታድርግ። ጭንቀቷን ታድምጥ። የራሷ አድረጋ ለህሊናዋ ትመግበው። በመንፈስ አዎን ምንጊዜም በመንፈስ ከእሷ አትለይ ቃል ናት አንቺም __**ከቃል ተማሪ**__ ይለኛል። ይለኛል ... ይለኛል ... ይለኛል" ...*

*የእኔ እናት ራዕይሽ ሚዛኑን ይዞ ያፋጥጠኛል። ፊት ለፊቴ ሆኖ „**መሆንን ቻይ።** ማለትን አሽቀንጥረሽ ጣይ፡ ግፊ እሷ ለአንቺ በአራት ማእዘን ጥብቆ ...መዘርጊያ መቆሚያ መቀመጫ በሌላት ተቀምጣ! ወዮ! እንዴት ላስረዳሽ በእሷ የደረሰውን ፍዳ!?*

እንዲያው መላወሻ በነሳት፤ ... ያቺ የሚሊዮን አዝመራ በእንጉቻችር አለቃ በሩ ተከረቸመባት ... እጥፍጥፍ ብላ በዛ ስልግ ባለው አንጀቷ ድፈት ብላ አፈር ላይ **ቃልሽ ወድቃለች ... ማተብሽ ትቢያ ነስንሳ የቀራንዮን መከራ ትቀበላለች።** ድረሽላት ... ድረሽላት ... ድረሽላት" ... ይለኛል። ይለኛል ... ይለኛል ... "

„ሥርጉት ብሎ" ይጠራኛል ወይ ስለው ደግሞ ... „ትሰሚያለሽ" ይለኛል አዎን ስለው ... „ከልብ አድምጪ እንዳትረሻት ... **ጢፍሽን እዳትረሻት** ... ለአፍታ አደራ! እንዳትረሻት ምልከቷን መልቲ እንዳይወስድ እና እንዳይነግድባት ሁነኛ ሁኚ ...!"

„መቆምሽ ለእሷ ከአልሆነ ከቶ ለማን ሊሆን ነው? ... እ - እ - እ - እ - እሷ ምጥ ላይ ናት ቀን ... ተደፈቶባታል። በፋሽስት እጅ ናት ወይ ጉድ! ... መሬቱ ዳፍንት፤ ጣሪያው ጠቀራ፡ ግድግደው አፉን ከፈቶ የስጋት ወላፍ የሚተፋ ... ያቺ፤ የምታውቂያት ወርቅ በሰንሰለት ሞገድ ላይ መሆኗን እንዳትዘነጊ ... ለአፍታ እ - እ - ...

አቤት! አቤት! አቤት! የአለባት መስቃ፤ ግልምጫ፤ መቼስ ቻይ አይደለች ችላው ነው እንጂ ... አቤት! ችሎታዋ! እንዲያው ለመሆኑ ከብረት ቁርጥራጭ ብረቱካን ተሰረቶ አይተሽ ታውቂያለሽ? አዎ እሷ የተሰራቸው ከነገርኩሽ ነው። **ለጋዋ ... ሀሞቷ ኮስታራ ነው። ቀጥ ... ያለች ቀጥተኛ። ደግሞ ግልጥ ንጥር ... የአናብስት ፋና!**

የሚገርምሽ አፍንጫዋ ባይተነፍስ ይሻሉ። ጉደኞች፤ የጉድ ጉድጋዶች እኮ ናቸው በፈጣሪ ጥበብ ሁሉ ይሳለቃሉ። ቁማ መከራዋን መቀበሏ፤ አይበገሬነቷ፤ ፅናቷ እያደር እየፈለቀ ... መሄዱን ሲያስቡት ድግሞ ያ ...ማቸዋል። አሁን እነዚህ ከሰው ተርታ ሊመደቡ ይሆን .. ይሀውልሽ ... እሷ ይህን ሁሉ ችላ ነው የተቀመጠችው።

በዓይናቸው ቢገድሏት በወደዱ። መንፈሷን ህሊናዋን ቢደበድቡት በፈለጉ ... ለነገሩ ማንን ፈርተው? የቀን ጅቦች አይደሉ ሆድ አደሮች። **የበቀል ሙሽሮች! ይሁዳ!**" ይለኛል ... ይለኛል ... ይለኛል ...

ይኸውልሽ ...

የእኔ ኪዳን በማዕልት እና በሌሊት እኔን ብቻ መሰለሽ ለእልፎች በየቤታቸው እየሄደ ዕራዕይሽ ያፋጥጣል። አይደከመው። ሰረጎ - ገቦች፡ እንዳይበሉኝ የሚለው ፈሊጥ ደግሞ ሰሞኑን አምጥቷል። ግን እናትዬ ጤናሽንስ እንዴት ነሽ? ያቺ በመቁንን የተለካቸው ጊዜ እና አንቺ እንዴት እና እንዴት እየተኳኳናችሁ ነው? አይዞሽ ብቻሽን አይደለሽም የእኛንስ ተይው ሰውነቱ

ሕይውቱ ያላቸው የንፁኃን ፀሎት ከአንቺው ጋር ነው። መንፈስ ቅዱስም ይጠብቅሻል።

አንደ ነገር የነገርሽን አሳታወስኩት ... ባለፈው ጊዜ „ እንወጣ ይሆን እያለን እናስብ" ነበር ብለሽኝ ነበር። አሁንም አሱን ታሰቢ ይሆን? ሆድሽ አይባባ አትሰቢ፡ **የሃልዬ አምላክ የት ሄዶ?!** የራሄልን እንባ የታደገ አምላክ **የእምዬን እንባም ይታደጋል**። እንደ ጨለመ አይቀርም። እንደ ደመነም አይቀርም። **ይነጋል ... በያነጋል**

ብርቴ ብረቱ እኔ በመዳህኒዓለም ሙሉ እምነት አለኝ አያዞሽ። አራዊቶች የልባቸው መድረሱን ሲያረጋግጡ እንደ ጦር የፈሩት የአንቺን ስመ ጥርነት፡ ሕዝቡ ለአንቺ ያለው ፍቅር፤ ዘመኑም እራሱ ያከበረሽ መሆኑን አይተው ሰጉ። የስጋት ዳፍነት ባፍ ጢማቸው አዳፋቸው። ያው እንደምታውቂው የልባቸውን ሲያደርሱ ከፍትፍት ያለውን ቀዳዳቸውን በደበሎ ከሸጓጎጡ እና ከወታተፉ በኋላ ... እንደ አመላቸው ምክንያት ፈልገው ... የሚሊቱን ይላሉ ... ያወ ጋሬጣ ብይናቸውን ... በእብለት ሞሽረው ብቅ ያደርጉታል።

ለነገሩ እነሱም ቢሆኑ ሰለ ቅንጣቷ ደቂቃ ምን ሥልጣን አላቸው ... ምንስ ዋስትና አለቸው ... ይናዳሉ ... ፈርኦን ወይንስ ሄሮድስ ማን ኖረባት ይህቼን የድንኳን ሥልጣን አይዞሽ ... ከምንም እና ከማንም በላይ የሁሉም ዳኛ ኤልሻዳይ አምላክ ፍርዱን ይሰጣል። ደግሞ ለቅን!!! **እማ ቅንዬ አንቺማ ከፍሉ ነሽ።**

ደግሞም ምንም አትይም ... ት-ኖ-ራ-ል-ን አለሽ። እ-ን-ገ-ና-ኛ-ል-ን። አምላካችን ተስፋችን ... መልሶ ይሰጠናል። አቤት ያን ጊዜ ስንገናኝ ከግፉ ሰንሰለት ከድቅድቁ አሳርሽ ገፈትረሽ ስትወጪልን ከቶ ምን እንል ይሆን ...? ለዛውም በተቋም! አዎን አንቺ እኮ ተቋማችን ነሽ። እመቤቱ ዓላማሽ ዓላማቸው ያደረጉ ሺህ ሠራዊቶችሽ እኮ ከአንቺው ጋራ ናቸው። እንደ አንቺው ጨላማ ተፈርዶባቸው በአይሁዳን እጅም ናቸው።

አንች ቅን ላስላሴ  የአሰሩ ኑሮሽ መሮሽ፡ አታከቶሽ፡ ሳለ እኔም ድግሞ ተጨምሬ አለፋሁሽ አይደለ? ስለ አደከምኩሽ ይቅረታ። አይዞሽ። በርችልን። ሁሉም እንደ መከሊቱ  ከአንቺ ጋር ነው። ጎግ ማንጉትም እንደ ጉም በኖ ይጠፋል አትጠራጠሪ ...  የእጁን ያገኛል ... ዕወነት ብትቀበርም መውጣቷ ግን አይቀሬ ነው። የቡላማዋ ኩረት ካብ ይናዳል ...

በይ ያን ቀንበጥ የፍቅር ተሚጋች ለቴድ ለድንቁንም የከበረ ሰላምታ አቅረቢልኝ። ደግሞ ምክንያት ካልፈጠሩ ዓይን ዓይን ልንገናኝ ጥቂት ቀናት ነው የቀረን ..

የሠራዊት ጌታ ልዑል እግዜብሄር በቃችሁ ይበለን። አሜን!

**የሃልዬ እናት አውራ የንብ**

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ግሩም ድንቅ

ዬአናብሰት ብርቅ

ፍልቅልቅ

***<u>የፅናት ወርቅ።</u>***

የሚያፈልቅ

ድምቀትሽ ዘሊቅ

መዳህኒት ታላቅ

የርትሀ ፍልቅ

ሚዛንን አልቅ

የሀቅ ዝንቅንቅ

***<u>ኢትዮጵያዊነትን አድምቅ።</u>***

ላንችስ አልልም ዝም

የእናቴ የቁርጥ ቀን ግንብ፣

የአንድነታችን ድባብ ....

የሃልዬ እናት አውራ ንብ።

አርያ ነሽ ቆራጥ እህት

***<u>ብርቴ የምግባር አናት</u>***

የትህትና ልዩ ቤት!

*ስጦታ፣ ለሃልዬ ሚዲቅሳ*

*ታህሳስ 27 ቀን 2001ዓ.ም ሄርሽን ሆቴል*

**ሃልዬን እንሰባት**

*ሥርጉተ ሥላሴ*

የተፈረደባት እናት ሀገር። የጨለመባት እናት ምድር። የደመነባት ቀዬ ኢትዮጵያ።
እመ - ብዙኃን ቅድስት ሀገር ታመሰች። ተሰለቀች። በልጆቿ እንባ ቆሰለች።
አዎን ... ከፅንሰቷ ጀምሮ የአሳርን የዕትብት ጡጦ ተቀልባ፣ ዕንባን ሰንቃ
ያደገችው የሦስት ዓመቷ ሀልዬ ከማንኛችንም በላይ በፋሽስቱ የበቀል ገጀሞ
የተከተከተች መከረኛ ህፃን ናት።

የሃልዬ ዬማዕልቱ የስጋት - የፍርሃት - የሰቀቀን ዕንባ ግን ዋጋ አለው። የእዮርን
አደባባይ ያንኳኳል። ንጉሡን እስከ ዙፋኑ መዳህኒዓለም እንዲታደገው በዓፅህኖት
ይጠይቃል።

የሃልዬ ዓይኖች የፋሽስቱን የፖሊስ ኃይል አረመኔነት መስጥሮታል። ጮርቃ
ሀሊናዋ የፈርዖንን አስተዳደር ... በፅንስ ሳይቀር የሚገመድሉ የጫካ አራዊቶች
ስለ መሆናቸው በጥቁር መዝግቦታል። የእናቷን ጡት ሳትጠግብ የእናቷን ፍቅር
ለቃሊቲ ነፍሰ በላዎች ሰንሰለት መዳረጉ የጠቅላይ ሚ/ሄሮድስ መለስ ዜናዊ ፍርድ
ከሰማዩ ዳኛ እንዲሰጥ በዕንባ ይማፀናል።

የሃልዬ የሰቀቀን ህቅታ የእናቷን ፍቅር እንዳታገኝ ከአቻወቿ ተነጥላ በስጋት፣
በጥርጣሬ፣ በፍርሃት የእንግልት ሰንሰለት መዋለሉን የሚመለከት -
የራሄልን ዕንባ የታደገ አምላክ ፍትህ ይልክ ዘንድ አበክሮ ያስገነዝባል።

በዚያች በመቁንን በተፈቀደላት ቁርጥራጭ ደቂቃ እናቷን ስታይ ብርቴ ብላ
ፍልቅልቅ ብላ ሮጣ ሄዳ በእናቷ እቅፍ ቆይታ ግን ነገር ግን በምድር ፈላጭ-
ቆራጮች ገደብ ተደርጎባት ዓይኖቿ ከርተት እያሉ ሳይጠጋገቡ ሲለያዩ ...

... ተገፍታ እንደ አዋቂ ስትወጣ፣ የሚያበሩ ዓይኖቿ ከስለው-ዕንባን አዝለው
ኮሶ ቆርጥማ ... መላ አካሏ ደምኖ ... ፈዞ፤ ... መንፈሷ ጥቁር ቀሚስ ለብሶ
... እግሮቿ አንድ ስንዝር ከቃሊቲ ፈቅ ማለት ተስኖት አሻም፣ አታዥኝም
ብሎ ሲሟገታት የተመለከተ አምላክ በጭራቆች ላይ ፍርዱን ይሰጣል።
ርትህ - ርትህ - ርትህ፣ እያለ በጉንጮቿ የሚወርደው ፍል ፍላሎት አንድ ቀን
ቀን ይወጣለታል ... ተስፋ መቸስ አያለቅም እና ...

አንድም ማዕልት በሰላም ውሎ በማያውቀው ሠፈሯ ያለው አዬር እራሱ አስፈሪ ነው። በመሆኑም እየባባች እንድትኖር ተገምድሎባታል። በሰቀቀን እንድትኖር ተገዳለች። ይህ የሃልዬን የህሊና ጓዳ የመሳጠረልንን ጎርበጥባጣ ጉድ መፍትሄ ያሰጣት ዘንድ ቀንበጡ ህሊናዋ ፍፁም ያልተገባውን ተሸክሟል እና ጠበቃዋ- ዋቢዋ-ሁነኛዋ እንሁንላት። ለዓለም ዓቀፉ የህፃናት መብት አስከበሪ ኃይል አቤቱታዋን እናሰማላት።

በር ሲከፈት እና ሲዘጋ የሃልዬ ህሊና የሚያስበው ፖሊስን ብቻ ነው። እናታቸው በነፃነት ከተቀመጡ ልጆች ጋራ ስትሆን የእኔ እናት ብርቴ እስር ቤት ናት በማለት ***ሥነ-ልቦናዋ ላይ የተነጣጠረ ድምፅ አልባ ቦንብ ነው።***

በዓለም ዙሪያ ያሉ ልጆች እና እናቶችም ለጭንቀቷ ፈጥነው ይደርሱላት ዘንድ ... በተደሞም አመሳጥሮለናል።

*ሃልዬን እንሰባት* - **ሳቅ ያጣች ህፃን**

*ሃልዬን እንሰባት* - **ስጋት ወተቷ የሆነ ህፃን**

*ሃልዬን እንሰባት* - **የወያኔ ሰለባ የሆነች**

*ሃልዬን እንሰባት* - **በማዕልት እና በሌሊት መንፈሷ በወንበዴ የፖሊስ ኃይል የሚዳፋ ህፃን**

*ሃልዬን እንሰባት* - **የቤተሰብ ፍቅር የተነፈገች ህፃን**

*ሃልዬን እንሰባት* - **ከፅንሷ ጀምሮ ነፃነቷን የአጣች ህፃን**

*ሃልዬን እንሰባት* - **ኩርምት፣ ጭብጥ፣ ድቅቅ፣ ስብርብር ብላ በራሷ ቋንቋ ህማማት ላይ ያለች ህፃን**

የምናከብራችሁ የድህረ ገፃአችን ታዳሚዎች ስለ ሃልዬ እንኳን አንድ ዓለም ዓቀፍ ተግባር ለመፈፀም እባካችሁ እንሰናዳ ....

*ለህፃናት መብት እንታገል!!*
*ህፃናት የመንፈስ ሀብል ናቸው!!*
*ትውልዳዊ ድርሻችን እንወጣ!!!*

**ያቺ ድሪ**

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ያች ድሪ
ያልሆነች ፈሪ
ተስፋነን ዘሪ።

ያች ዕንቁ
የህግ ዕንቁ
ሃሰትን አውልቁ።

ያች ጀግና
ያላት ዝና
የተግባር መና።

ያች ፈርጥ
የአንስት ጌጥ
ሃቅ እምትንጥ።

ያች ተፈሪ
ፍቅርንን አድሪ
ፅናትን አብሪ።

ያች ፍቅር
የትግሉ ገበረ
የመስዋትነት አድባር።

ያቺ ደፋር
የቆራጥነት መንበር
ፍሬ ዘር።

ያቺ ነፍስ
ቅዱስ መንፈስ
እንባን አበስ።

… 20

ያች ብርቴ
የዕውነት ዕትብቴ
የትግስት ሚተቴ።

ያች ህብስቴ
የአርነት ምልክቴ
የሴቶች ክብርቴ።

አንበሳዋ እህቴ
የእኩልነት ሚተቴ
የፍፁም ታማኝነት ፏፏቴ

*ጥር 12 ቀን ሄርሽን ሆቴል*

*ሥጦታ ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ  የአንድነት ሊቀመንበር*

## የነጠረው ወርቅ የቅዱስ መንፈስ ጥበቃ አይለዬውም

****

*ከሥርጉተ ሥላሴ*

ወርቅን ማንጠር እንጅ መዳብ ወይንም ነሃስ ማድረግ አይቻልም። ወርቅን ቢቀብሩት እንደ ተፈጥሮው እንጂ ከተሰጠው መክሊት ውጪ ዝገ ወይንም በልዞ አይገኝም። በፍፁም! በፍፁም! በፍፁም! በፍፁም! በፍፁም ....

**አዎን** ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅስ የአንድነት ሊቀመንበር  የዘመኑን ንፐር ወርቅ ወካይ ናት። አረመኔዎች ባልተወለደ አንጀታቸው የሚደርሱባት ግፍ እና በደል ሆነ ህሊናዋን ስልብ እንዲሆን የሚደርጉት ኢሰባዊ ድርጊት የፀጋቸዋን ወርቅነት አይለውጠውም።

የወያኔ አስተዳደር በማዕልት እና በሌሊት የሚያሰደድረው የተላያዬ የህሊና ቶርች ሆነ ቅጥቀጣ የበለጠ ወርቅቱን ያነጥረዋል እንጂ ከቶውን ማድያት አያለብሰውም! ....ዳኛ ብረቱካን ሚዲቅሳ የምትከፍለው መሰዋእትነት በሕሊናዋ በተመሰጠረው የፀና ህዝባዊ ፍቅር - ኃላፊነት መንጭቶ ነው እና፤ ... የሚንገበገብላት ሕዝብ ፀሎት እና ምህላ ሆነ ዬዬሰዓቱ እሰቤ መንፈሳዊ ዕሴት አለው።

በአንደ ወቅት ጋዜጠኛ ኤሊያስ ክፍሌ ሲነገሩ እንደ ሰማሁት ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ከዳኛ ብረቱካን ይብልጠሉ እሳቸው ምን አለቸው ቦንብ የላቸውም፤ ፕሬዚዳንቱ ግን ቦንብ አላቸው ብለው ነብር። ባልሳሳት እ.አ.አ ግንቦት 22 – 2009 በከረንት አፈርስ ዲስከሽን ፎረም በነበራቸው የቃለ ምልልስ ክፈለ ጊዜ ... ነበር ይህን ቃል የተናገሩት ...

ይህ በእውነት የማስተዋል ዝንፈት፡ ግድፈት ይመስለኛል። ነብዩ እግዜብሄር ዳዊት በመዝሙሩ „ ሀገርን ህዝብ ካልጠበቀ ሠራዊቶች በከንቱ ይደክማሉ’ ይላል አዎን የሠራዊት ኃይል መመከት የሚችል ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜ በሰለጠነ አካኋን የመጡባትን ጠላት ድል ነሰታ ነፃ አፈሪካዊት ሀገር መሆን ባልቻለች ነበር።

በራሱ በእኛ ትውልድ እንኳን ደርግ የነበረው ሠራዊት፡ የጦር መሪዎቹ ብቃት፡ የመሳሪያው ዓይነት የአፍሪካን አህጉራዊ ጦር ይወክል ነበር። በብዛትም በጥራትም ጥንካሬውም ቢሆን የዚያኑ ያህል ... ነበር። ግን ነገር ግን ከዚህ ግባ ለማይባል የሚካ ሠራዊት ተረታ ትጥቁንም ፈታ ... ይህ በራሱ ሰፊ የጥናት እና የምርምር ሥራ የሚሰራበት ስለሆነ ለባለሙያዎች ልተወው።

ብቻ የተነሳሁበት .....መሰረታዊ አውራ ጉዳይ ወያኔም ሆነ መሰል አመለካከት ያለቸው ወገኖች የተሰወረባቸው አንድ ትልቅ ሚስጢር ያለ ይመስለኛል። እሱም <u>ከክብርት ዳኛ ብረቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር ጋር ስለ አለው የቅዱስ መንፈስ ጥበቃ</u> ይህን ብዙዎቹ ይዘሉታል። ይስቱታል። አዝናለሁ። በእውነት አዝናለሁ። ልቤ በረመጡ ይረገበገባል - ይንገበገባልም።

... እንደ እኔ ከጠቅላይ ሚ/ ሄሮድስ መለስ አስተዳደር ይሁን ከፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት ሠራዊት በላይ የብርቴ ቅዱስ መንፈስ ይበልጣል! ይለቃልም! ይመራልም! ባይ ነኝ። ይህን ስል በይመስለኛል አይደለም በእርግጠኝነት እንጂ ... ይህን የተገለጠላቸው ወይንም ፀጋው የተሰጣቸው ወገኖች ብቻ በአንድምታ ሊያነቡት፡ ሊተረጉሙት፡ ሊያምሰጥሩት ይችላሉ።

እንደገናም ከብርቴ ጋር አብሮ የታሰረው ወገን በጥራትም በመጠንም ያይላል። ዕልፎች በመንፈስ አብረው ታሰረዋል። በመዳህኒዓለም ዘንድ አንዷ ጠብታ ዕንባ ደግሞ ዋጋ አላት። እንኳንስ የዕልፎች ...

ስለዚህም የፈለገ ዓይነት ድርጊት ቢፈፀም መንፈስን በማላሸቅ አእምሯን ከጥቅም ውጭ ለማድረግ ቢሞከር እኔ ግን በአንደ ነገር በጣም እርግጠኛ ነኝ በፈጣሪዩ ጥበቃ፤ ጽናቷ ፈልቆ ፈተናውንም ድል እንደሚያደርግ ፈፅሞ ጥርጣሬ የለኝም።

ከክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የአንድት ሊቀመንበር ጋር ያለው ቅዱስ መንፈስ ህሊና ... አይታመም! አይዝልም! አይሞትም! ይልቁንም ዳግም አብቦ ጎምርቶ እናዩዋልን። ደገሞም ብቻውንም አይደለም ....

ወርቅን ለማዛግ መታገል ሆነ መፈታተን የህሊና እውርነት ነው!

የሰማዩን ፀጋ ፅናትን፤ ሰው ሰራሽ ፈተና አይበግረውም!

አራት ዓይናማው መንገዳችን ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው!

**አንብላ አደራ!**

****

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ሀሳብ አባትሎ ተልልትሎ ሊበላኝ

ናፈቆት አብተክትኮ ሊጎርሰኝ ሲሻማኝ

አንደበትሽ ርቆ በምናብ ሲናገረኝ

ትህትናሽም መጥቶ ፅናትን ሲጎርሰኝ
እንዳንችም እንዳንችም መሆኑ ተሳነኝ።

ጨለማው ጨለማው ጨላመው
ውውውውውው
እንዴትስ ይዞሻል?
እንዴት ያደርግሻል?
የትግል መሪያችን
ምሳሌ እህታችን
እንድምን ሀነሻል።

ናፍቆቱ ናፍቆቱ
ቱቱቱቱቱቱ
ስስቱ ስስቱ
ቱቱቱቱቱተ
የቀለጥሽበቱ የት ይሆን መንገዱ?

ሰንሰለት ሰንሰለት
አንችን በሰንሰለት!
ዋቤን በሰነሰለት!
ሀቅን በሰንሰለት!
ቃልን በሰንሰለት!
በበቀል በስለት።

አንተ ወንድሜ ሆይ!
አንች እህቴ ሆይ!
እባካችሁ ...
አቤት! በሉ ወደ ላይ።

ቀለብትህ ታስሮ ----
ቀለበትሽ ታስሮ ----
ኩርምት - ጭብጥ ብላ
እርር - ጥወልግ ብላ
እንቡጥ ስታነባ
አብረጎትም አንባ!
ዝም አትበይ አንቢ!
ለእሷ ተንገብገቢ።

ህልሟን እንጋራ!

አንበላ አደራ!

*ሥጦታ ... ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዴቅሳ የአንድነት ሊ/ቀንበር*

*ሀምሌ 9 ቀን 2001 ዓ.ም ሲዊዘርላንድ*

## መራሂት

*ከሥርጉተ ሥላሴ*

ሴት ብልህ ናት። ሴት ቆራጥ ናት። ሴት አርቆ አሰቢ ናት። ሴት ፍቅር ናት። ሴት ጥበብ ናት። ሴት ብቁ አስተዳዳሪ ናት። ሴት እናት ናት። ሴት እሩህሩህ ናት ሴት አዛኝ ናት። ሴት ለራህብ ደራሽ ናት። ሴት ጭንቅን ተጋሪ ናት። ሴት አጽናኝ ናት። ርህርትት ሴት ብሩህ ናት። ሴት ሚሰጢር ናት። ሴት ጀግና ናት። ሴት እውነት ናት። ሴት ማህባረዊት ናት።

ሴት ከእናትነት ፀጋዋ ጋር ሰፊ የሆነ መክሊተ ፀጋ በፈጠራት አመላክ ተሰጥቷታል። እኔ በግሌ ቀደም ባለው ጊዜ በዜና ስከታተል ከነበረኝ አክብሮት ይለቅ በአካል ክብርት ዳኛ ብረቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር ሳይ ከላይ የዘረዘርካቸውን ጥልቅ ፆታዊ በረከት አይቻባታለሁ።

ዘመን የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል እንዲሉ ... ያን የመሰለ ለዛ አና ውበት መራሂተ እኩልነት ወያኔ ቀራኒዎ አዋለ። ጨለማ በዬነ። ፋሽስትነት ማለት ከዚህ በላይ ምንድን ሊገልጠው ይችል ይሆን? ያን ማይጠገብ አንደበት በሰንሰለት' ... ያን የመረሂነት ብቃት በተስፋ መጠት ጉድጓድ፤ ያን የመሰለ የቁርጠኝነት ትህትናዊ ሰላማዊ ጉዞ እንቅፋት ፈጠረለት ... ነጎድጓዳማው በረዶ በተውልዶ ተሰፋ ላይ ማቱን አወረደ ......

በምንም ዓይነት መሰፈርት ክብርት ዳኛ ብረቱካን ሚዲቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር የተሰጣት ስልታዊ የመሪነት ጥበብ ብልሃት የሚመዝን አንስት ለእኔ ህሊና አላገኘሁለትም። ድንቅናት። በወጣትንት፤ በአፍላነት እንደ ጎልማሳ፤ እንደ ሃይኖት ትክክለኛ አባቶች። ሽበታቸው በውስጣቸው እንደበቀለው አዛውነታት በመቻቻል በማስማመት በማለስለስ ለህግ የበላይነት ታግሎ ማታገል የታደለች ....

ሴቶች በእውን የምንለብሰው፤ የምንጫማው፤ የምንተኛበት፤ የምነጓዝበት፤ ደላን ይሆን አካላችን እግርብርት ሆና። አንዲት ልጅዋ እና ደካማ እናቷ ለበላሃሰቦች ትታ፤ ለእኛ እንዲህ ሲትንገበገብ ስትገፈተር፤ ሲትገፉ፤ ሲትለበለብ በግለምጫ ሲትወቃ እጃችን አጣምረን እንቀመጥ ወይንስ አጋራነታችን በተግባር እናስጊጥ ... የቱ ይሆን ምርጫችን?!

የማከብራችሁ እህቶቼ ....

በእውነት እንቁረጥ በሁሉም መስክ ተግተን እንታገል። ቀዳሚ ዋስ ጠበቃ ለመሆን የፊት ረድፈኛ እንሁን እባካችሁን? እራሳችን በማስተወል ሆነን አንጠይቅ አዎ ያቼ ፍልቅልቅ ... ጨለማ ውስጥ ... ዳፍንት ውስጥ በጨካኞች እጅ ነገ ምን ያደርጓት ይሆን ... ነፍሳችን እናባትላት።

ሩኃችነን ፋታ አሳጥተን ለተግባራዊ ተሳትፎ እንተጋ ዘንድ ለህሊናችን እንፍቀድለት፡፡ እንዲጠይቀን እንዲያፈጥጠን፡፡ የክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የከፉ ቀኗዋ ዋቢ እንሁን፡፡

የፆታ ፀጋችን ለፀረ ወያኔ ትግል እናውለው፡፡

ፅናትን የመገበን ወርቅ ይደምቃል እንጂ ፈጽሞ አይወይብም!!

እስኪ አሁን ደግሞ በጸጋዬ ድህረ ራዲዮ "ከውረሰ ጽናት" ዝግጅት አንድ ፕሮግራም ብቻ በምልሰት እንቃኝ፡፡

ዬካቲት 29 ቀን 2002 ዓ.ም ዝግጅትን፡፡ ይገርማል ልክ 2001 ወርሃ መስከረም የውርሰ ጽናት ዝግጅት ተጀመረ፡፡ ልክ በዓመቱ መስከረም ብርቴ ተፈታች፡፡ የጥቅምት ወርህ የመጀመሪያ ፕሮግራም በምልሰት የአንድ ዓመቱን በጥቂቱ ቃኝቶ አሁን ወደ መደበኛ ፕሮግራሙ ተመለሰ .... ተመሰገን፡፡

**አንቺ የቃል ባለ ቀንበር**

*ሥርጉተ ሥላሴ*

የዛሬ ዓመት አንችን አሰቤ
ከአጋሮቼ ጋር ተሰባሰቤ
ስናከብርሽ ስናነሳሳሽ
ስናወሳሳሽ

ዘንድሮ ከእኛ ጋር ትሆኚ ብለን ነበር
ዕልም ነበረን
አዎን ብልን ነበር አለመን
ታዲያ ምን ይሆናል ... ተሰፋችን ተመንጥሮ
ነበር ብቻ በነበር ተቀመሮ
ህልማችን አሮ ተኮማትሮ
ዛሬም አንቺ ከዛው ነሽ
ከድቅድቁ ቤትሽ
በበለሃሰቦች እጅ ነጻነትሽን
ተነጠቀሽ **ተቀመትሽ**

እግርሽ ሲፈልግ
ሲያማትብ ...
ህሊናሽ ርትህን ሲመኝ ሲለካ ...
መንፈስሽ ለህግ የበላይነት ሲመሳን ሲመዘን ...
ጥልቅ ተፈጥሮሽ ፍቅር ሲመግብ
ታይቶሽ ነበር፤ ነበር .... ነበር
**አንቼ የቃል ባለ ቀንበር፡፡**

ንጹህ ዓየሯን ጨበጥኩ ብለሽ ነበር
ውድ መሆኗን ግን አጣቅሰሺ
ነግረሽን ነበር ...
ለግል ነፃነት የታገልሽ
ያታገልሽ
የአርነት ብቁ ወታደር!
በእኩልነት ገበር
በወጣትን ፈል ድንበር
ቃልን በቃል አስተጋብረሽ
አሰተባብረሽ ቃልን መርተሽ
በመሆን ቀምረሽ
አንቺ የሐቅ **ቃል ባለ ቀንበር።**
**እንቁ**
**ብቁ**
ህግን ልታውይ ልታሰከብሪ በአድባር
ደግመሽ እንደገና ተዳርግሽ ለእስር
አይዞሽ እህት ዓለም
የተስፋችን ልዩ ዓለም

እጹብ
እጹብ
ድንቅም ድንቅ
ብርቅ

የተግባር ደማም
የጽናት ሐዋርያ የትውልድ ድፍረት ናኝ ..
የአንስት ቁንጮ የመንፈሴ ዜማዊ ሰናይ
ዜና
አናት ዋና
ገናና!
ህማማት ላይ ሁነሽ
መካራ “ምታይው
አንቺ ውዱ ጀግና
ብቻሽን ታፈንሽው;

ያልፈልን ስትዥው

አሸፈረኝ አለ

እሱ ባለ ጊዜ ምን አለ! ምን አለ!

ዬዬማዕለቱ ጉድ እርር ኩምትር ያደረግል ለትውልዱ አዲስን ዕራይን ሰንቃ አዲሷን ኢትዮጵያ በምናቧ እየዳሰሰች እጅግ ጥልቅ በሆነ ስሜት እና ፍላጎት እራሷን እረስታ ለዛች ለምታከበራን ለምታሰከብርን ለታላቋ ሐገር ስትማስን ተጠለፈች ...

አደረጓት ጥልፍ

አርበኝነትን ስትጠልፍ፣

ሐቀን በወረቅ ሰተዘመዝም

በጀግንነት ስታስማማ

ሰትነብይ ያላት ግርም፣

ልታበቅል ለእማማ  ዘንባባ!

እሷም እራሷ ዘንባባ

የወስጥ ሙዳይ የከፉ ቀን

የእንባ ዋቢ ዘብ አደር፣

የትውፊት ልዩ ሀር

ውብ ነገር

የብልህንት መሰረት ሥር

የፍቅር ማግ ድር።

ሰላምን አቅፋ ደግፋ ሰላምን ጠርታ ዓውጇ ሰላማን አናገራ እሷን እራሷን አንተርሳ ሰላምን ናፈቃ ሰላምን አክብራ ልታውል በአድባር ለራብ ማዕድ ሰርታ ታዲያ ምን ይሆናል በመሰሪ ተጠለፈች በአራዊት መንጋ ... በዛ የጥፋት መንጋጋ ... ተወጋች ተሰቅዛ።

ልታነጋ ስትወጋ

ዝም ብለን እናውጋ

ያ ቺ ንብ

ህዝብ

የነጻነት ደም

ታማመች አለች እምም

ጥሪ ላከች በእትብት ለእትበት እንዲሆኑላት ዋቢ ጠበቃ... ላከች ጥሪ ንቧ፣ የተግባር የመርህ ሰፈፍ ድረሱ በነፍስ አለች ተማጸነች ድምጾን ሰጠች ... ውል ውል ውል ለውል እንድንበቃ ቃል እንድናስር ቃል እንድንሆን ለእውነት እንድንተጋ

እውነትም አውነት ነች

ፍሬ ዘሯ እውነት

ማሰዋ ሃቅ ነው

ምርጥ ሰብል አምራች፤

የእውነት ጉልላት

ምዕላት

የዕትብት ዕትብት ነች ...

ድረሱልኝ ያለቸው እኮ ወገኖቼ ... መከራዋ ቢይል ፍዳዋ ቢበዛ መገፋቷ ቢንር ነው። ህልሟ ቢያስገድዳት ቢያነሳ ቢጥላት ህምም ላይ ወደቀች። ድረሱልኝ አለች የሐቅ ጠበቃዋ ወጣቷ ፍልቅልቅ የቃል አርበኛዋ ....

ለሚመራመሩ

ተፈጠሮዋ እንደዚህ በቋንቋ በፊደል እንዲህ ማነገሩ

የብርቱካን ፍጥረት ጥልቅ ነው ሚሲጢሩ፤

እስኪ እናንተ ሆዬ እሷኑ ሆናችሁ

ቃሊቲ ሄዳችሁ

ወጥታችሁ ወርዳችሁ

ያችንን ጠባብ በር - እሷኑ እያያችሁ

በግልምጫ ፈረስ እዬተለጋችሁ

በበቀል በቋሳ እየታመሳችሁ፤

ጨለማም ቀኑ አብሮ ሲያሳዳችሁ

ዘመን አልቀረበት - እሱም ቢያገላችሁ

የጠገበ ሁሉ እንዲህ ቢለጋችሁ

አሮጌ እናታችሁ በመጢሪያ ሰዓት ቢንገላቱባችሁ

የማትርቃት ፍሬ በወላጇ ናፍቆት ብተወቃባችሁ

ይህ አልበቃ ብሎ

ቢታወክ ጤናችሁ

ለመታከም እንኳን ፈቃድ ቢነሷችሁ

ትችሉት አላችሁ? ? ? ! ! !

አዎን የክብርት ዳኛ ብርቱካን ስቃይ እና መከራ ከዕለት ዕለት እዬበረከት እዬሰፋ እዬከፋ እዬሄደ ነው። እኛ ደግሞ ሻማ በማበራት ብቻ ተወስነን ባለንበት ታቱ ጅግራ ስንል የከፉት ነገሮች ሁሉ እዬቀደሙን ነው። ተሎ መደረስ ያለብን ይመስለኛል። አብሶ የምትችሉ ሰዎች ጠንከራችሁ ልትሰሩ ይገባል ባይ ነኝ ምክንያቱም የተከበሩ ፐ/ አስራት ወ/ እጣ ፋንታ በክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ ዬአንድነት ሊቀመንበርም ላይ እይንፀባበ ነው። ለነገሩ የክብርትነቷ ጉዳይ እኮ በባለቤትንት ዬያዘው ኃይል እንብዛም ነው ...

አሁን ደግሞ ሌላ ከባድ ዘግናኝ ሁኔታ ፊት ለፊት ተጋርጧል የሚሰጣት መዳህኒት የሚመደበላት ሃኪም ሁሉ በጣም አሳሳቢ ነው። በርትተን ልንሰራ ይጋብል።

የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ሲዊዘርላንድ ቢንተርቱር



ፍቅር ነሽ
እውነት ነሽ፤
ዬእኛ ጉልላት - ንጋት ነሽ።